# በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር

## የ2014 በጀት ዓመት የ10 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

## ለህዝብ ተወካዮች ምክር-ቤት የቀረበ

ግንቦት 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


**1. የቁልፍ ተግባራት አፈፃፀም ........ 2**
1.1 የዕቅድ ዝግጅት ........ 2
1.2 ፈፃሚና አመራሩን ማዘጋጀት ........ 3
1.3 ባለድርሻ አካላትን ማዘጋጀት ........ 3
1.4 የሰው ኃይል ልማት እና ግብዓት ማሟላት ........ 4
1.5 የሪፎርም ተግባራት አፈፃፀም በተመለከተ ........ 4
1.6 የማስፈፀሚያ ህጎችን በተመለከተ፡- ........ 5
1.7 የትራንስፖርት እና ሎጆስቲክስ ዘርፍን የማዘመን ሂደት ........ 6

**2. የአበይት ተግባራት አፈፃፀም ........ 8**
**2.1 የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ዘርፍ ........ 8**
2.1.1 የትራንስፖርት አገልግሎት ........ 8
2.2.2 የሎጆስቲክስ ዘርፍ ........ 10
2.2.3 የባቡር ትራንስፖርት ........ 12
2.2.4 የአቪዬሽን ዘርፍ ........ 12
**3. የዘርፈብዙ ጉዳዮች ........ 13**
**4. የበጀት አፈፃፀም ........ 14**
**5. የኦዲት ሪፖርት ........ 14**
**6. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች፣ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ........ 15**
6.1 ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ እርምጃዎች ........ 15
6.2 ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ........ 15

**የተከበሩ የኢፌዲሪ ሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈ-ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት**

**ክቡራትና ክቡራን፣**

በቅድሚያ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት የ10 ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለተከበረው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዳቀርብ እድል በማግኘቴ በመላው የሥራ ባልደረቦቼ ስም ምስጋና ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና መልሶ በማደራጀት በአዋጅ 1263/2014 የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት መነሻ በማድረግ ዋነኛ ተልዕኮው የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በመቅረጽና ሥራ ላይ በማዋል የኢኮኖሚ ዕድገትን የሚደግፍና የሚያፋጥን፣ተደራሽ፣የተቀናጀ፣ቀልጣፋ፣አስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትራንስፖርት ስርዓት በመዘርጋት የህብረተሰቡን ፍላጎት በማሟላትና ዘርፉ ለሀገር ዕድገት የሚጠበቅበትን ሁሉ እንዲያበረክት በማድረግ የህዝባችንን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ይህንንም ለማሳካት ፍኖተ ብልፅግናን ለማረጋገጥ ከተዘጋጀው የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ጋር ተናባቢ የሆነ የትራንስፖርት ዘርፍ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ በማቀድ ለተግባራዊነቱም በዋነኛነት የአስፈፃሚና የፈፃሚ አካላትን አቅም በመገንባት እና ህብረተሰቡን በማሳተፍ መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴዎች በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡
በዚህም መሰረት የዘርፉን ዋነኛ ተልዕኮ ከማሳካት አኳያ ባለፉት አስር ወራት የተከናወኑ ተግባራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እንደሚከተለው አቀርባለው፡፡

## 1. የቁልፍ ተግባራት አፈፃፀም

### 1.1 የዕቅድ ዝግጅት

ከፍተኛ አመራሩ የበጀት አመቱን እቅድ አፈጻጸም በተፈለገው ደረጃ መተግበር እንዲቻል ለዕቅድ ዝግጅቱ ልዩ ትኩረት በመስጠት "አፍሪካዊ የብልፅግና ተምሳሌት" የመሆን ሃገራዊ ራዕይ የሰነቀውን የትራንስፖርት ዘርፍ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ተጠሪ ተቋማትን እና ክልሎችን በማሳተፍ ቴክኒክ ቡድን እና አብይ ኮሚቴ በማቋቋም የዝግጅት ሂደቱ በጥብቅ ዲሲፕሊን እንዲመራ በማድረግ በየአመቱ በሚገባ የተሸነሸነ በመሆኑ የ2014 ዕቅድ ከዚሁ በመቅዳት እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡በሂደቱም የፖሊሲ፣ስትራቴጂና እቅድ አፈፃፀም መነሻ በማድረግ እንዲሁም ቀጠናዊ፣አህጉራዊና ዓለም ዓቀፋዊ ጉዳዮችን በሚገባ በመዳሰስ፣የዘርፉ ወሳኝ ሰብአዊና ቁሳዊ ሀብቶች እና በዓለማችን ብሎም በሀገራችን ወቅታዊ የትራንስፖርት ፍላጎት እይታ ለውጥን ለመቃኘት ጥረት ተደርጓል፡፡

ከዚህም ባሻገር የትራንስፖርት ዘርፉ በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተካሄደ ላለው የኢኮኖሚ ሪፎርም በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የተቀመጡ የትኩረት አቅጣጫዎች እና ፕሮጀክቶችን ታሳቢ በማድረግ እና በማስተሳሰር የተዘጋጀ ሲሆን ተደጋጋሚ የሆኑ ውይይቶችን በማድረግ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ እና ግብዓት በማሰባሰብ የዳበረ ዕቅድ የተዘጋጀ በመሆኑ በጠራ ዕቅድ ወደ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገር ተችሏል፡፡

በትራንስፖርት ዘርፍ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ እና የዘርፉ የ5 ዓመት ውጤት ተኮር /BSC/ ዕቅድ መሰረት የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ዕቅዱ ተግባራዊ ሲደረግ በተሟላ መልኩ ዉጤታማ መሆን እንዲቻል የፊዚካል ዕቅድን ከፕሮግራም በጀት ጋር በማስተሳሰር እና ተቋማዊ የመፈፀም አቅምን ከማሳደግ አንፃር ዋና ዋና ስትራቴጂካዊና ተቋማዊ ተግባራት በዕቅዱ የተካተቱ ሲሆን በትኩረትና በክትትል የሚተገበሩ ይሆናል፡፡

### 1.2 ፈፃሚና አመራሩን ማዘጋጀት

የትራንስፖርት ዘርፍ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት ሂደት እና ውይይት በተመለከተ የ2013 በጀት ዓመት አፈፃፀምን ከሁሉም የተቋሙ ሰራተኞች፣ከክልልና ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮዎች፣ከተጠሪ ተቋማት፣ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ፣ ከትራንስፖርት ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ካውንስል እና ከትራንስፖርት ወርኪንግ ግሩፕ በአጠቃላይ 14,820 ሰራተኛና ባለድርሻ አካላት ጋር በመገምገም ጠንካራና ደካሞ ጎን በመለየት በ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ውስጥ በሚገባ በማካተት ዕቅድ የተዘጋጀ ሲሆን በየደረጃው በማወያየት እና ግብዓት በማሰባሰብ የጠራ ዕቅድ በማዘጋጀት ለአፈፃፀሙም ሁሉም የየድርሻውን ወስዶ መፈፀም እንዲችል የጋራ መግባባት እና ግልፅ የሆነ አቅጣጫ ማስቀመጥ ተችሏል።

ለዘርፉ ከተዘጋጀው የ5 ዓመት ቢኤስሲ ዕቅድ ላይ የ2014 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር ዕቅድን በመውሰድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ጨምሮ ለ10ሩም ተጠሪ ተቋማት እስከ ግለሰብ ፈፃሚ ማውረድ ተችሏል።

ከትራንስፖርት ዘርፍ የ10 ዓመት መሪ የልማት እቅድ ካስኬድ የተደረገውን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ለመተግበር የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ዕቅድ/ቼክሊስት በማዘጋጀት እና የክትትልና ድጋፍ ቡድን በማዋቀር የዕቅድ ዝግጅት ጥራት፣እስከ ግለሰብ ስለመውረዱ እና የአፈፃፀም ስልቱን በመከታተል እና በመደገፍ ወደ ስራ መግባት ተችሏል።

### 1.3 ባለድርሻ አካላትን ማዘጋጀት

ባለፈው በጀት ዓመት የትራንስፖርት ዘርፍ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅዱ እና ከዚህ ካስኬድ የተደረጉ የ5 ዓመት እና የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ ከ69 የትራንስፖርት ዘርፍ የአገልግሎት ማሻሻያ ካውንስል አባላት ጋር ውይይት ለማድረግ ታቅዶ ከ69ኙ አባላቱ ጋር ውይይት በማድረግ የዕቅዱን 100% በመፈፀም የተደራጀ ግብዓት በመስጠት ለዕቅዱ መዳበር የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ መደረጉ ይታወቃል።በዚህም መሰረት ለ2013 በጀት ዓመት የታቀዱ ተግባራትን በሚገባ በመገምገም ለ2014 ዕቅድ ዝግጅት ግብዓት በግብዓትነት ተወስዷል።

የአገልግሎት ማሻሻያ ካውንስል አባላት የራሳቸው ዕቅድ አፈፃፀም እንዲያቀርቡ በማድረግ እና በጋራ በመገምገም የ2014 በጀት ዓመት የካውንስሉን ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ተደርጓል፡፡ይህም ባለድርሻ አካላት እና የካውንስሉ አባላት ለዕቅዱ ባለቤት በመሆን ከመጠየቅ ባሻገር የጋራ ውጤት ለማምጣት የሚተጉም ጭምር እንዲሆኑ እያስቻለ ይገኛል፡፡

### 1.4 የሰው ኃይል ልማት እና ግብዓት ማሟላት

የሰው ኃይል ማሟላት እና የዓቅም ግንባታ ሥራዎችን በመስራት ለትግበራ ከማዘጋጀት አንፃር በዘርፉ በአጠቃላይ ለ2224 አመራርና ሰራተኞች ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ1860 ሰራተኞችና አመራሮች ስልጠና በመስጠት የእቅዱ 83% ማሳካት ተችሏል፡፡

### 1.5 የሪፎርም ተግባራት አፈፃፀም በተመለከተ

ቀደም ሲል ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ተጠሪ የነበረው የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ስልጣንና ሀላፊነት ለትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የተሰጠ በመሆኑ ተቋሙን ከሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ጋር ለማዋሀድ ባሳለፍናቸው ወራት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር እና የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን መዋሀድን ተከትሎ የአደረጃጀት እና መዋቅር ጥናት በማካሄድ እና በማፀደቅ የሰራተኛ ምደባ ተከናውኖ የተጠናቀቀ ሲሆን የተመደቡ ሰራተኞችን በሙሉ በተለያዩ የስልጠና ርዕሶች አዲስ አስተሳሰብ ለላቀ አገልግሎት በሚል መሪ ሀሳብ በአፍሪካ የልህቀት ማዕከል በማሰልጠን ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል፡፡ሥልጠናዎቹ የመፈፀም ዓቅምን የሚያጎለብቱ፣በቡድን የመስራት ባህልን የሚያዳብሩ እና የሀገር ወዳድነት እና የአገልጋይነት መንፈስ የሚያላብሱ ሲሆኑ ከለጋሽ ድርጅቶች ድጋፍ በማፈላለግ ምንም ዓይነት መደበኛ በጀት ሳይነካ ሥልጠናው በመስጠት በተሸለ ዝግጅት መዋቅሩን ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል፡፡
ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሁለቱንም ተቋማት በጀት ለማዋሀድ አዲሱን አደረጃጀት ተከትሎ የበጀት ፕሮግራሞች በመቅረፅ እና በገንዘብ ሚኒስቴር በማፀደቅ የቀድሞ የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን እና የትራንስፖርት ሚኒስቴር በጀት እንዲዋሀድ ተደርጎ ከአንድ ቋት መጠቀም ተጀምሯል፡፡

### 1.6 የማስፈፀሚያ ህጎችን በተመለከተ፡-

የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ማቋቋሚያ ደንብ፣ስለ ተሽከርካሪ መኪኖች ክብደትና ልክ መወሰኛና መቆጣጠሪያ ደንብ፣የባለሞተር ተሽከርካሪዎች ፍጥነት ወሰን ደንብ፣ የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ እና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ደንብ ፀድቀው ወደ ተግባር የገቡ ሲሆን የመንገድ ትራንስፖርት ረቂቅ አዋጅ ደግሞ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ታይቶ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተመርቷል፡፡

ከሪፎርሙ ጋር በተያያዘ ባሳለፍናቸው ወራት በቀድሞ የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ሲሰጡ የነበሩ አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ እና የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ ለማድረግ ለክልሎች፣ለከተማ አስተዳደሮች እና ለተለያዩ መስሪያ ቤቶች 11 አገልግሎቶችን በውክልና በማውረድ ተግባራቱን በዕውቀት ለመምራት እንዲያስችል የሥልጠና ማንዋል በማዘጋጀት ለክልል የዘርፉ አመራሮች እና ባለሞያዎች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

የአስፈፃሚ አካላትን እንደአዲስ መደራጀት ተከትሎ ዘርፋችንን ለሚደግፈው እና ለሚከታተሉ የተከበሩ የከተማ መሰረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት በትራንስፖርት ዘርፍ የህግ ማእቀፎች፣ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች፣የ10 ዓመት መሪ የልማት እቅድ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ካውንስል በተመለከተ፣የልማት አጋሮች እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ሞደርናይዜሽን እንዲሁም ተቋማዊ ሪፎርም ላይ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ የተሰራ ሲሆን በዚህም መሰረት ቋሚ ኮሚቴው ዘርፉን ተረድቶ ተቋማችንን በግብረ መልስ፣በመስክ ምልከታ እንዲሁም ወደ ምክር ቤቱ የተመሩ የህግ ማዕቀፎችን ባለድርሻ አካላትን እና የሚመለከታቸውን አካላት በማወያየት እንዲዳብር በማድረግ ተቋማችንን እየደገፈ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ ለተቋማዊና ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በርካታ ሥራዎች የተሰሩ ሲሆን የ30 ዓመት የትራንስፖርት ማስተር ፕላን በማዘጋጀት የመጨረሻ ምእራፍ ላይ መድረሱ፣2000 ኪ.ሜ የመንገድ ደህንነት የግምገማ ጥናት መጠናቀቁና ቀጣይ እርምጃዎች መጀመራቸው፣የትራንስፖርት ዘርፍ አለም አቀፍ የአማካሪ ቡድን (International Advisory Council) መቋቋሙ እንዲሁም ከአጋር አካላት/Transport working group/ እና ከትራንስፖርት ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ካውንስል ጋር ያልተቆራረጠ ግንኙነት በማድረግ አፈፃፀሞችን የመገምገም እና የልምድ ልውውጥ ማድረጉ ዘርፉን ለማዘመን እና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

## 1.7 የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ዘርፍን የማዘመን ሂደት

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ዘርፍ በቴክኖሎጂ የዘመነ እና የተቀላጠፈ አገልግሎት ለህዝባችን ተደራሽ ለማድረግ የሚያከናዉናቸዉን ተግባራት ለማሳካት የሚረዳ ተቋማዊ እና የተደራጀ የዳታ ማዕከል በመገንባት ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል፡፡ይህ የመረጃ ማእከል የሚኒስቴር መ/ቤታችንን የዉስጥ አሰራሩን ለማዘመን የወረቀት አልባ የአሰራር ስርአት ለመገንባት ከማስቻሉም በላይ የሚኒስቴር መ/ቤታችን እና ተጠሪ ተቋማት እንዲሁም ክልሎች በጋራ እንዲጠቀሙበት እና በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የመረጃ ሥርዓት እንዲኖር በማሰብ የተደራጀ ነዉ፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ የሚስተዋለዉን የአሰራር ክፍተት በዘመናዊ የአሰራር ሂደት ለመለወጥ የሚደረገዉን ጥረት በከፍተኛ ሁኔታ የሚያግዝ ይሆናል፡፡

ዲጂታል ስትራቴጂ ለኢትዮጵያ ብልፅግና /ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025/በዝርዝር እንዳስቀመጠው ሀገራችን እጅግ ዘመናዊ በሆነ፣በቴክኖሎጂ በታገዘ አካሄድ በመራመድ በ2025 የምትደርስበትን አቅም ስንመለከት ለተግባራዊነቱ እጅግ መትጋት የሚያስፈልግ መሆኑና በዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ውስጥ የትራንስፖርት ዘርፉም የበኩሉን በመወጣት እንደ ሁልጊዜው ለኢኮኖሚው የጀርባ አጥንት ሆኖ እንዲቀጥል ያስችለዋል፡፡

በዘርፉ የሞደርናይዜሽን ሲስተም መዘርጋቱ፣የትራንስፖርት አገልግሎቶች በኢንተርኔት መረብ አማካኝነት አገልግሎቶች እየተሰጡ በመሆናቸው 74,173 የህብረተሰብ ክፍሎች በኢንተርኔት አገልግሎት ያገኙ ሲሆን አገልግሎቶቹ ቴክኖሎጂን በመጠቀም መሰጠታቸው ጊዜና ገንዘብን ከመቆጠብ እና አላስፈላጊ እንግልቶችን ማስቀረት አስችሏል፡፡

የትራንስፖርት ዘርፉ በዘመናዊና በተቀናጀ የመረጃ አያያዝና ልዉዉጥ ስርዓት ባለመደራጀቱና በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ባለመደገፉ ምክንያት በተለያዩ ዉስብስብ ችግሮች እንዲዋጥና ከኢኮኖሚዉ እድገት ጋር የሚመጣጠን እድገት ለማስመዝገብ ከፍተኛ እንቅፋት እያጋጠመዉ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ ከችግሮቹ ውስጥም በዋነኝነት የሚጠቀሰው በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮችን ለማስቆምም ሆነ ለመቀነስ የሚያግዝ ከሰው ተፅዕኖ ነፃ የሆነ የዳበረ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ የመረጃ ስርዓት አለመኖር ነው፡፡

ስለሆነም ከላይ የተገለፀውን ፍላጎት መነሻ በማድረግ እና የነባሩን ሲስተም ክፍተቶችን ማሻሻል ላይ ተመርኩዞ የተቀናጀ የትራንስፖርት ዘርፍ መተግበሪያ ስርአት ከሚያጠቃልላቸው አበይት

ስራዎች ውስጥ አንዱ የተቀናጀ የጭነት ትራንስፖርት ማስተባበሪያ ስርዓት በቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ኢንስቲትዩት አልሚነት በልፅጎ በመጠናቁ ወደ ተግባር ማስገባት ተችሏል፡፡

ይህ ሲስተም ቀድሞ የነበረው ሲስተም ጉድለቶች እንዲቀርፍ እና ያላካተታቸውን ወሳኝ የዘርፉ ስራዎችን አካቶ ዲዛይን ከመደረጉ ባሻገር ዘመኑ የሚጠይቀውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ትኩረት አድርጎ ዲዛይን መደረጉ የቀድሞው ሲስተም ላይ የነበሩትን ችግሮች ሙሉ በሙሉ በመቅረፍ ቀጣይ የሚመጡ የቴክኖሎጂ ለውጦችን በቀላሉ እንዲቀበል እና ከባለድርሻ አካላት ሲስተሞች ጋር ለምናደርገው የመረጃ ልውውጥ በቀላሉ መስማማት እንዲችል አድርጎታል፡፡

ዝርዝር አገልግሎቶቹን ስንመለከት በጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ መሰማራት የሚፈልጉ ግለሰቦችና ባለሃብቶች አዲስ የትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጫ ለማውጣት፣ዓመታዊ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማደስ፣ወደ ጎረቤት ሀገራት የንግድ የትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ አሽከርካሪዎችና ረዳቶች የድንበር ተሻጋሪ የአሽከርካሪና ረዳት መታወቂያ ለማውጣት፣ለማሳደስና ምትክ መታወቂያ ለማግኘት ደንበኞች በአካል መምጣት ሳይጠበቅባቸው አገልግሎት ማግኘት ያስችላል:: በዚህ ሲስተም በአሁኑ ወቅት በጠቅላላው 20 የጭነት ኦፕሬተሮች 542 የጭነት ተሽከርካሪዎች ሲስተሙን ተጠቅመው የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ያመለከቱ ሲሆን በዚህም መሰረት በመስተናገድ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎትን ከማዘመን አንፃር የኢቲኬቲንግ ሥርዓትን ከነበረው ወጥ የክፍያ ስርዓት /fixed tariff/ ወደ ፌርማታን መሰረት የአደረገ የአከፋፈል ሥርዓት በመቀየር በአራት የታክሲ መስመሮች አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል፡፡

የጉዞን መረጃ በቀላሉ መያዝ የሚያስችል የጉዞ መስመር አመላካች በ460 የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አውቶብሶች ላይ መግጠም ተችሏል፡፡

በማሪታይም አስተዳደር አገልግሎት ከ4000 በላይ የመርከብ ካፒቴኖች፣መሀንዲሶች እና ሌሎች ሞያተኞች የሚሰጠው አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በአካል ሳይገኙ ባሉበት ቦታ ሆነው/online/ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ አገልግሎቱን መስጠት ተችሏል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት**

የአበይት ተግባራትን አፈፃፀም በተመለከተ ሚኒስቴር መ/ቤታችን ተጠሪ ተቋማትን በማስተባበር ለመምራት እንዲችል በርካታ የአሰራር ማሻሻያዎች በማድረግ ወጥ የሆነና ተከታታይነት ያለው የድጋፍና ክትትል ሥርዓት በመዘርጋት ቋሚ የግንኙነት ጊዜዎችን አስቀምጦ ስራዎችን በመገምገምና አቅጣጫ በማስቀመጥ ለመፈጸም ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በ10 ወራት ውስጥ የተከናወኑ የአበይት ተግባራት አፈፃፀም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2. የአበይት ተግባራት አፈፃፀም

### 2.1 የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ዘርፍ

#### 2.1.1 የትራንስፖርት አገልግሎት

- በሀገር አቋራጭ የትራንስፖርት አገልግሎት 460 ሚሊዮን ህዝብ ለማጓጓዝ ታቅዶ 417.1 ሚሊየን (91%) ተሳፋሪዎችን ማጓጓዝ ተችሏል፡፡
- የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት የተስፋፋባቸው ትላልቅና መካከለኛ ከተሞች ከ14 ወደ 18 ለማሳደግ ታቅዶ በ19 ከተሞች በማስፋፋት የዕቅዱን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡በዚህም የብዙሃን ትራንስፖርት የማጓጓዝ ድርሻ ከነበረበት ከ34% ወደ 37% ማሳደግ ተችሏል፡፡
- በዓመቱ በመንገድ ትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚደርሰውን የሰው ሞት በ10 ሺህ ተሽከርካሪ ከ32.6 ወደ 30 ዝቅ ለማድረግ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን ይህንንም ለማሳካት ከጳጉሜ እስከ ጳጉሜ እንደርሳለን፣መንገድ ለሰው፣የእግረኞች እና ብስክሌተኞች ቀን በሚል ርዕስ የሚዘጋጁ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የህብረተሰባችን ተሳትፎ ማጎልበቻ አማራጮችን በመጠቀም ለ38,434,067 ዜጎች ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ34,253,092 ዜጎች ወይም የዕቅዱ 89% የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡
- ከዚሁ ጋር በተያያዘ የመንገድ ደህንነት ሥራዎች ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የራሱ አድርጎ እንዲሰራበት ከማድረግ አንፃር ከግሉ ዘርፍ አካላት ጋር ውይይት ማካሄድ ተጀምሯል፡፡
- የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ አደጋ የሚበዛባቸውን ቦታዎች በመለየት በ10,067 ቦታዎች ላይ የመንገድ ምልክቶች፣የሴፍቲ መስታወቶች፤የእግረኛ

ማቋረጫ ዜብራ የመቀባትና የማቋረጫ ግንባታ፣የፍጥነት መገደቢያዎች እና ልዩ ልዩ አጥሮች እንዲተከሉና እንዲገነቡ ተደርጓል። በአጠቃላይ በተደረጉ ጥረቶች የትራፊክ አደጋ የሞት ምጣኔ ከአምና ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ6% መቀነስ አሳይቷል።

- ለፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት 19.5 ሚሊዮን ሰራተኞችን ለማጓጓዝ ታቅዶ 19.6 ሚሊዮን ሰራተኞችን ተጠቃሚ በማድረግ 100% መፈፀም ተችሏል።
- በፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚሰጥ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት 11.7 ሚሊዮን ህዝብ ለማጓጓዝ ታቅዶ 12.8 ሚሊዮን ተሳፋሪዎችን በማጓጓዝ 100% መፈፀም ተችሏል።
- በፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት ብር 693.8 ሚሊየን ገቢ ለማስገባት ታቅዶ ብር 693.8 ሚሊዮን ገቢ በማስገባት የዕቅዱን 100% መፈፀም ተችሏል።
- የሞተር ተሽከርካሪዎች 3ኛ ወገን መድን ሽፋንን ለማሳደግ 799,971 ተሽከርካሪዎች የመድን ሽፋን እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ 674,959 ተሽከርካሪዎች ሽፋን እንዲያገኙ በማድረግ 84% መፈፀም ተችሏል።
- በ10 ወራት ለመሰብሰብ ከታቀደው የፈንድ ገቢ ብር 84,800,000 ውስጥ 76,656,2000 በመሰብሰብ የዕቅዱን 90% መፈፀም ተችሏል።
- ሚስጢራዊነቱ የተጠበቀና በቴክኖሎጂ ለመጠቀም የሚያመች ተለጣፊ የመድን ምስክር ወረቀት 746,080 ለማሳተም ታቅዶ 746,121 ተለጣፊ (100%) ታትሞ ማሰራጨት ተችሏል።

### 2.2.2 የሎጆስቲክስ ዘርፍ

- የሃገራችን የሎጂስቲክስ ማነቆዎችን በመፍታት ዓለም አቀፍ የሎጂስቲክስ አፈጻጸም ደረጃችንን ለማሻሻል እና ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ እና አስተማማኝ የሎጂስቲክስ ሥርዓት ለመዘርጋት እንዲቻል በብሔራዊ ሎጂስቲክስ ፖሊሲ እና ስትራቴጂያችን የተለዩ ኢንተርቬንሽኖችን ብሔራዊ የሎጂስቲክስ ካውንስል በሚያደርግልን ድጋፍና አቅጣጫ ተጠሪ እና አጋር ተቋማትን በማስተባበር በዘርፉ እመርታ የሚያመጡ ሥራዎችን ለማከናወን ጥረት እየተደረገ ነው፡፡
- ገቢና ወጪ ጭነት በተመለከተ **15.06 ሚሊየን ቶን** ገቢ እና ወጪ ጭነት ለማስተናገድ ታቅዶ 11.09 **ሚሊየን ቶን** በማከናወን የዕቅዱን 74% መፈፀም ተችሏል፡፡
    - በሀገር ውስጥ በኮንቴይነር ሊታሸጉ የሚችሉ ወጪ ዕቃዎችን አሽጐ ከመላክ አኳያ በ10 ወሩ 65% ለማድረስ ታቅዶ 62.12% በኮንቴይነር አሽጎ በመላክ 95% መፈፀም ተችሏል፡፡ በተለይም ደግሞ የቡና ወጪ ንግድ ወደ 98% የሚሆነዉ በኮንቴይነር ታሽጎ ሙሉ በሙሉ በባቡር እንዲጓጓዝ በማድረግ የቡና ጥራት እንዳይቀንስ እንዲሁም ቅሸባ እንዳይኖር ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም እቃው ጅቡቲ ሄዶ ቢታሸግ በውጪ ምንዛሬ ሊወጣ የሚችል 2,069,662.5 ዶላር ወይም ብር 105,997,764.94 ወጪን ማዳን ተችሏል፡፡ከዚሁ ጎን ለጎን በአንድ ኮንቴይነር በአማካይ ለ14 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡
- አማካይ የመርከቦች የወደብ ላይ ቆይታ ከነበረው **15 ቀናት** ወደ **12 ቀናት** ለማድረስ ታቅዶ ወደ 9 ቀናት በመቀነስ ›100% መፈፀም ተችሏል፡፡
- በሃገራዊ ሎጂስቲክስ ስትራቴጂያችን በግልጽ እንደተቀመጠው የሃገራችንን **የባህር ወደብ አጠቃቀምን በማስፋት** የሎጂስቲክስ ወጪንና ጊዜን ለመቀነስ፣ በድምር ውጤቱም የሸቀጦች ዋጋ ንረትን በመቀነስ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ስትራቴጂክ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡

- ከዚህ አንጻር ከጅቡቲ ወደብ **ተጨማሪ የባህር ወደቦችን** ማለትም **ታጁራና በርበራን** እንዲሁም **ሞያሌን/ሞምባሳን** ለመጠቀም በተደረገው ጥረት፤ የሦስቱ ወደቦች የኢትዮጵያን ጭነት የማስተናገድ ድርሻ **ጭማሪ** ያሳየ ሲሆን፣ **በጅቡቲ ወደብ** ላይ የነበረውን አጠቃቀም በ14.62% መቀነስ ተችሏል፡፡ በእነዚህ ወደቦች በ10 ወሩ ወደ ሀገር ውስጥ የገባውን ጭነት የባህር ወደብ አጠቃቀም ድርሻ ስንመለከት **ጅቡቲ፡ 86%፣ ታጁራ፡ 9.16%፣ በርበራ፡ 5.0%፣ ሞያሌ፡ 0.02%** ሊሆን ችሏል፡፡
- በአጠቃላይ የሎጂስቲክስ ወጪን ለመቀነስ በበጀት አመቱ 10 ወራት በተከናወኑ በርካታ ስራዎች እና በተደረጉ ሰፊ ጥረቶች ብር 2.3 ቢሊየን ብር ወጪን ማዳን/መቆጠብ ተችሏል፡፡
- በሎጂስቲክስ ስትራቴጂው ከተቀመጡ የመፍትሔ ሀሳቦች /Incieatives/ በ9 ወሩ ለማከናወን ከታቀዱት 84 የመፍትሄ ሐሳቦች ውስጥ 46 የመፍትሄ ሐሳቦች ከ80%-100%፣28 የመፍትሄ ሐሳቦች ከ50% - 79% እንዲሁም 10 የመፍትሄ ሀሳቦች ከ50% በታች ተከናወኗል፡፡ በዚህም መሰረት የስትራቴጂውን አፈፃፀም በ9.85% ለማሳደግ በዕቅድ ተይዞ 7.24% በማከናወን የዕቅዱን 73.5% መፈፀም ተችሏል፡፡
- የብሉ ኢኮኖሚ Country Report (Baseline Study)ተዘጋጅቷል፣ከኢጋድ ጋር በመሆን የኢጋድ regional ብሉ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ በኢትዮጵያ መሪነት የተዘጋጀ ሲሆን ይህን መሰረት በማድረግ የሀገራችን ብሉ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፣የመርከቦች ምዝገባ አገልግሎት አደረጃጀት concept note እና ባቡር እና መርከብን በማቀናጀት ለመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል concept note ተዘጋጅቷል፡፡
- ሀገራችን በሎጂስቲክስ ያለችበትን ደረጃ ለመለካት /lojistics performance Index/ በዓለም ባንክ መስፈርት መሰረት ተጠንቶ ባለፈው ዓመት ከደረስንበት 2.51 በዚህ ዓመት መጨረሻ 2.6 ለመድረስ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- ባህረኞችን በውጭ ሀገራት ለማስቀጠር የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ የተዘጋጀ ሲሆን የመርከብ ባህረኞችን በማሰልጠን እና በውጭ ሀገራት መርከቦች ላይ በማስቀጠር በወር በአማካይ 750 ሺህ ዶላር ወይም በአስር ወራት 6.75 ሚ ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

### 2.2.3 የባቡር ትራንስፖርት

- በባቡር የተጓጓዘ የጭነት መጠን 1.57 ሚ.ቶን ለማጓጓዝ ታቅዶ 1.34 ሚ.ቶን በማጓጓዝ የዕቅዱን 85.5% ተፈፅሟል፡፡ከሚሰጡ የባቡር የጭነት አገልግሎቶች 1.35 ቢሊየን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 1.39 ቢሊዮን ብር ገቢ በማመንጨት የዕቅዱን 100% መፈፀም ተችሏል፡፡

- የባቡር ትራንስፖርትን የአገልግሎት አቅም ለማሻሻል በተደረጉ በርካታ ጥረቶች በ10 ወሩ የገቢ ብትን ጭነትን እንዲሁም የገቢና ወጪ ኮንቴነር ጭነትን በባቡር በማጓጓዝና የአገልግሎት ሽፋኑን በመጠናከር በገቢና ወጭ ዕቃ ትራንስፖርት 657.5 ሚሊዮን ብር የትራንስፖርት ወጭን ማዳን ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጅቡቲ ወደብ ይፈጠር የነበረ የኮንቴይነር ክምችት እና የዕቃዎች የወደብ ላይ ቆይታ ጊዜ እንዲቀንስ አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡
- በኢትዮ ጅቡቲ ባቡር መንገደኞችን ወደ ተለያዩ መዳረሻዎች ማጓጓዝ በተመለከተ በ10 ወራት 108 ሺህ መንገደኞችን ለማጓጓዝ ታቅዶ 124.67 ሺህ በማጓጓዝ 100% መፈፀም ተችሏል፡፡

- ከዚህ በተጨማሪ የመንገደኞችን ፍላጎት የበለጠ ለማርካት እንዲቻል የIntercity Passenger (Commuter) Transport ወይም በከተሞች መካከል የሚደረግ የመንገደኞች ትራንስፖርት ለማስፋፋት እንዲቻል ባሳለፍናቸው 10 ወራት በአዲስ አበባ - ጅቡቲ የባቡር መስመር በ4 ከተሞች የሚገኙ የባቡር ጣቢያዎችን በመክፈት አገልግሎት መስጠት ተጀምሯል፡፡

### 2.2.4 የአቪዬሽን ዘርፍ

- በአቭዬሽን ዘርፍ በ100ሺ በረራ የሚኖረውን የአውሮፕላን አደጋ (Accident) መጠን በዓመት ተቀባይነት ወዳለው ደረጃ ቁጥር 0.4 ማምጣትና በስታንዳርዱ መሰረት ለማስቀጠል ተችሏል፡፡

- ለ145 ነባር እና አዲስ አውሮፕላኖች የበረራ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት (Certificate of Airworthiness) ለመስጠት ታቅዶ ለ143 አውሮፕላኖች የበረራ ብቃት በማረጋገጥ 98% መፈፀም ተችሏል፡፡

- ለ7,176 ባለሞያዎች የአቪየሽን ላይሰንስ ለመስጠት ታቅዶ 7,238 በመስጠት የዕቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

- ከሲቪል አቪዬሽን አገልግሎት 2.3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለመሰብሰብ ታቅዶ ከኤርናቪጌሽን አገልግሎት 1.942 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ በመሰብሰብ የዕቅዱ 84% አፈጻጸም ተመዝግቧል፡፡

**3. የዘርፈብዙ ጉዳዮች**

- የትራንስፖርት ዘርፉ በተለምዶ ከሚጠቀመው የካርበን ነዳጅ አንጻር በሚያበረክተው ከፍተኛ የካርበን ልቀት የተነሳ ለከባቢ አየር ሙቀትና የአየር ብክለት የጎላ አስተዋጽዖ ከሚያበረክቱ ዘርፎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህንንም በመቀነስ በሃገራችን ዘላቂ እና ለአካባቢ ተስማሚ ትራንስፖርት ሥርዓት ለመገንባት ስትራቴጂ ቀርጸን ለተግባራዊነቱ ከአጋሮች ጋር በትኩረት እየሠራን እንገኛለን፡፡

- የሀገራችንን የትራንስፖርት ዘርፍ የሚያዘምኑና ከካርቦን ልቀት ነጻ የሆኑ፣ እንዲሁም እንደ ሀገር ለነዳጅ ምርት የምናወጣዉን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚያስቀሩ፣የተሽከርካሪ አይነቶችን ወደ ሀገራችን ማስገባትና ማስፋፋት አንዱ እና ዋነኛዉ የስትራቴጂያችን አቅጣጫ ሲሆን ይህንንም ለማሳካት የሚረዳ የሀገር ዉስጥ የተሽከርካሪ ኢንዱስትሪዎችን የመደገፍ ስራ በማከናወን ላይ እንገኛለን፡፡ ከዚህ አንጻር ከተከናወኑ ሥራዎች መካከል ጥቂቶቹን ለመግለጽ፡-

- በአማራጭ ታዳሽ የኃይል ምንጮች (በተለይም በኤሌክትሪክ እና በጸሐይ ኃይል) የሚሰሩ ተሽከርካሪዎችን በሀገራችን በማስፋፋት የህብረሰተሰቡ ጤና እንዲጠበቅና የኢኮኖሚ ልማት እንዲረጋገጥ የተያዙ ግቦችን ለማሳካት በሀገራችን **የታዳሽ ኃይል ትራንስፖርት ብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ** ተመስርቷል፡፡

- ከዚህም ጋር በተያያዘ ለመስኩ ፈር ቀዳጅ የሆነና **የመጀመሪያ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ቻርጅ ማድረጊያ ማእከል** እና **ሁለተኛ ሞዴል የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች መገጣጠሚያ ፋብሪካ** በይፋ ስራ ማስጀመር ተችሏል፡፡
- በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፍ በ10 ወራት **ለ81,500 ዜጎች የሥራ እድል** ለመፍጠር ታቅዶ **ለ72,017** የዕቅዱን (**88%**) ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡
- በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል በተከሰተው ጦርነት **ለተፈናቀሉ ዜጎቻችን** ዘርፉችን አጋርነቱን ለመግለጽ ተጠሪ ተቋማትን እና አጋሮችን በማስተባበር፡-
- በአማራ ክልል ደብረብርሀን እና ባህር ዳር፣በአፋር ክልል ሰመራ በመገኘት በአጠቃላይ የ26.9 ሚሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ እና 1.5 ሚሊየን ብር የሚያወጡ የተለያዩ ቁሳቁሶች በአካል በመገኘት ድጋፍ ተደርጓል፣

## 4. የበጀት አፈፃፀም

በ2014 በጀት ዓመት 10 ወራት ለሚኒስቴር መ/ቤታችንና ለተጠሪ ተቋማት በአጠቃላይ ብር **882** ሚሊዮን በጀት ተመድቦ **731.9** ሚሊዮን ብር ጥቅም ላይ በማዋል የበጀቱን **83%** መጠቀም ተችሏል፡፡

## 5. የኦዲት ሪፖርት

የሚኒስቴር መ/ቤታችን እና የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት የ2013 በጀት ዓመት ኦዲት ምርመራ ተከናውኖ ከግኝት ነፃ ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ ሌሎች ተጠሪ ተቋማት የሂሳብ ምርመራ ተጠናቆ ሪፖርት እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

## 6. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች፣ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

### 6.1 ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሔ እርምጃዎች

#### 6.1.1 ያጋጠሙ ችግሮች

- የወጪ ምንዛሪ እጥረት፣
- የፀጥታ ችግር መኖር፣
- በትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች ላይ የሚካሄድ ስርቆት፣

#### 6.1.2 የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

- የውጪ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በጋራ በመስራት ስፖንሰር በማፈላለግ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- የመሰረተ ልማቶች ላይ የሚካሄድ ስርቆት እና የፕሮጀክቶች መጓተት ለመቅረፍ ከዩቲሊቲ ተቋማት፣ ከክልል መስተዳድሮች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ ይገኛል፣

### 6.2 ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- ቅንጅትና ትብብር ማጠናከር፣
- የዕውቀት ሽግግር እና የአቅም ግንባታን አጠናክሮ ማስቀጠል፣
- ዲጂታል የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የመንገድ ደህንነት ስራዎችን በተቀናጀ መልኩ በመስራት የትራፊክ አደጋ እንዲቀንስ ማድረግ፣
- በዘርፉ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳደግ መስራት፤
- ቴክኖሎጂን በመጠቀም የትራንስፖርት ዘርፉን ማዘመን፣

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት**

ለማጠቃለል በበጀት ዓመቱ 10 ወራት የዘርፉን የአደረጃጀት፣የአሰራርና የሰዉ ኃይል ጉድለቶችን በማስተካከል፣የግል ባለሀብቱን ተሳትፎ በማሳደግ፣የተቀናጀ የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽነትን የማሳደግ፣የሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን የማረጋገጥና የማዘመን፣የትራፊክ ደህንነትና ማኔጅመንትን የማሻሻል እንዲሁም የትራንስፖርት ዘርፍ ለአየር ንብረት ለውጥ ያለውን ጫና የመቀነስ እና ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አቅም የመፍጠር ግቦችን በመያዝ የዘርፉን ተጠሪ ተቋማት እና የክልል አካላትን በሰፊው በማሳተፍ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወንን እንገኛለን፡፡ በቀጣይም በዘርፉ ልዩ ትኩረት ለሚሹ ጉዳዮች ቅድሚያ በመስጠት፣ በመልካም አሰተዳደር እና በአገልግሎት አሰጣጥ በቴክኖሎጂ በመታገዝ እና ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓትን በመዘርጋት በዘርፉ ስር ነቀል ለውጥ ማምጣት ይጠበቅብናል፡፡ ስለሆነም የተከበረው ም/ቤት እና ቋሚ ኮሚቴው የተለመደ ትብብራችሁና አጋርነታችሁ ለጋራ ውጤታማነታችን እንደማይለየን በመተማመን እስካሁን ለተደረገልንም ትብብር በሚኒስቴር መ/ቤታችን ስም ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

**አመሰግናለሁ!!**